# የአሜሪካን መንግስት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ምን ዶለው?

ሸረፋ ከድር

Ksherefa@yahoo.com

ከመሰንበቻው ሲያሻው የአመፅ ድቤ የሚመታው፣ በል ሲለው ደግሞ ሽብርተኞች ሀገራችን ውስጥ እንዳሻቸው ይፈነጩ፡ ዘንድ በመመኘት የፀረ-ሽብር ህጉ እንዲሰረዝ የባጥ የቆጡን የሚለፍፈው "አንድነት" የተሰኘው የቀለም አብዮት ናፋቂ ፓርቲ የሊቀመንበር ምርጫ አካሂዶ ነበር። ድምፅ ከሰጡት 256 ሰዎች ውስጥ የተከበሩ የፓርላማ አባል አቶ ግርማ ሰይፉ /የፓርቲውን አባላት ወይም በእኔ እምነት ስውር መራጭ ወይም አስመራጭ ሆኖ የተገኘው የአሜሪካ መንግስትን ምን እንዳስቀየሟቸው ባላውቅም/ 29ኙ ብቻ የማስተዛዘኛ ድምፃቸውንና ይሁንታቸውን ቸረዋቸው ተሸንፈዋል። በአንፃሩ ደግሞ በምርጫ 97 ወቅት በምርጫው ዕለት አዲስ አበባ ላይ "ምርጫው ተጭበርብሯል" ብለው ጠዋት ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መግለጫ ሰጥተው፣ ወዲያውኑ ረፋዱ ላይ ከረባታቸውንና ሸሚዛቸውን እንኳን በቅጡ ሳይቀይሩ "ተሳስቻለሁ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ" በሚል በአቋም የለሽ የዥዋዥዌ ፖለቲካ ተጫዋችነታቸው የምናውቃቸው ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በ227 ድምፅ ሊቀመንበር ተደርገው ተመርጠዋል።

እርግጥ ኢንጂነሩ በምርጫ 97 ወቅት ምንም እንኳን 'ቅንጅት የተሰኘው የጎዳና ላይ ነውጠኛ ቡድን ሳጥናኤል ከሚባለው የሰይጣን አለቃ ጋር ተባብሮ አሳሳተኝ' የሚል ዓይነት ድምፀት ያለው 'ይቅርታ' ቢጠይቁም፤ በወቅቱ አዲስ አበባ ላይ ይኸው ነውጠኛ ቡድናቸው ማሸነፉ ሰውዬው ማቅ ለብሰውና ማቅ መስለው የሃፍረት ሻማን ሊከናነቡ ችለዋል። አዎ! ምርጫው በመካሄድ ላይ ሳለና መራጮች ወደ ምርጫ ጣቢያ አቅንተው ሳያበቁ ብሎም ድምፅ ቆጠራው እንኳን ሳይጀመር ሰውዬው ገና ከማለዳው በሐሰተኛ መሲህነት በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው 'በአንድ ራስ ሁለት ምላስ' መሆናቸው በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ መሳቂያና መሳለቂያ መሆናቸው የሚዘነጋ አይደለም። ነገረ-ስራቸው "የቅሌት ቀን አይመሽም" እንዲሉት ዓይነት ነበር ማለት ይቻላል።…

…ምንም እንኳን ኢንጂነሩ ምርጫው በመካሄድ ላይ ሳለ አስቀድመው ይህን ያሉትበት ዋነኛ ምክንያት በወቅቱ ሀገራችን ውስጥና ውጭ ከነበሩ የቀለም አብዮት አራማጆች የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ለማስፈፀም እንዲረዳቸው መደላድል ለመፍጠር መሆኑ

በገሃድ የሚታወቅ ቢሆንም፤ ሚዛናዊውና ፍትሐዊው አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ ይህን በቀለም አብዮት በአቋራጭ የስልጣን እርካብን ለመቆናጠጥ ያለመውንና በንፁሃን ደም ቤተ-መንግስት ለመግባት ሌት ተቀን በነውጥ ሱባኤ የሚፀልየውን የሁከት ቡድን ሊቀበለው አልፈቀደም። ህገ-መንግስቱንና በደሙ ዋጅቶ ያመጣውን ስርዓት በህግ የበላይነት ሊያስከብር ችሏል። በአንፃሩም ከአፈጣጠሩ ጀምሮ የፀረ-ዴሞክራሲያዊነትንና የፀረ-ህዝብነትን ቀኖና ያንበለብል የነበረው የነውጥ ቡድኑ፤ ከተወሰኑት አባላቱ በስተቀር ፓርላማ ባለመግባት እንዲሁም ያሸነፈበትን የአዲስ አበባን መስተዳድር ባለመረከብ ድምፅ በሰጠው ህዝብ ላይ አላግጦበታል።…

ውድ አንባቢዎቼ! እንዲያው ለነገሩ የአንድነት ፓርቲ ወረፈኛ ሊቀመንበር የኢንጂነር ግዛቸውን ፖለቲካዊ “ማንነት” እና  እምነት ለግንዛቤ ያህል በትውስታ መልክ ቀንጭቤ ምርጫ 97ን አነሳሁት እንጂ፤ የወጌ ዋነኛ ማጠንጠኛ በሰሞነኛው የአንድነት ፓርቲ ምርጫ ላይ በስውር መራጭነት አሊያም በአስመራጭነት ስለተገኘው የአሜሪካ መንግስት አስገራሚ ሁኔታ ነው። ታዲያ ይህን የሚያስገርም ድርጊት ከማውሳቴ ፊት በቅድሚያ ኢንጂነሩ ስለ ተመረጡበትና የተከበሩ አቶ ግርማ “ባሸንፍም እንኳን ንግግር የማደርግበትን ወረቀት ይዤ አልመጣሁም” በማለት አስቀድመው እንደማያሸንፉ ስላወቁበት አሊያም ስለተነገራቸው የምርጫ ውጤት አንድምታ ጥቂት ለማለት ወደድኩ። …

…አዎ! በእኔ እምነት የምርጫው ውጤት ሁለት ነባራዊ ሃቆችን የሚያመላክት ነው—የፓርቲውን የታወቀ ማንነትና የወደፊት ፍላጎቱን። እርግጥም አንድነት የቅንጅት ነውጠኛ አመራር የነበሩትን ግለሰብ መሪው አድርጎ መምረጡ ፓርቲው ለሁከት ተግባር ምን ያህል አክብሮት እንዳለው የሚያሳይ ነው። ሰውዬውን ከተከበሩ አቶ ግርማ ይልቅ ይሻሉኛል ብሎ በሰፊ የድምፅ ልዩነት እንዲመረጡ ማድረጉም ከነውጥ ጋር የካቶሊክ ጋብቻ የፈፀመ ነውና ለዚህ እኩይ ምግባሩ የሚመጥኑትን አሊያም “የተሻለውን መጥፎ” የመረጠ ይመስለኛል።

ኢንጂነሩ በምርጫ 97 ወቅት የነበራቸው የነውጥ አመራር “ተሞክሮም” ተመራጭ አድርጓቸዋል ባይ ነኝ። ለነገሩ የተከበሩ አቶ ግርማ ፓርቲውን በአመራር ደረጃ የተቀላቀሉት በቅርቡ በመሆኑና ከወረቀት ላይ ያልዘለለ የሁከት “ተሞክሮ” ብቻ ያላቸው በመሆኑ ከኢንጂነር ግዛቸው ጋር ሊወዳደሩ አይችሉም። የምርጫው ውጤት የጥንቸልና

የዔሊ ሩጫ እስኪመስል ድረስ በስፋት የተሸነፉትም ምክንያት ለዚሁ ይመስለኛል– ፓርቲው የጎዳና ላይ የነውጥ ልምድ የሌለውን አይፈልግምና። የተከበሩ አቶ ግርማም ቢሆኑ "ፓርቲ ለመምራት ብዙ የሚቀረኝ ቦታ እንዳለ ተረድቻለሁ" ማለታቸው ከዚሁ አንፃር ያለባቸውን ክፍተት ወደፊት ለመሙላት ፍላጎት እንዳላቸው እየነገሩን ሳይሆን አይቀርም። ግና ለዚህ ፅሑፍ አቅራቢ የሁለቱ ግለሰቦች የምርጫ ፉክክር (ሶስተኛው ተፎካካሪ "ባልታወቀ ምክንያት" ወይም "ተመራጩ ማን እንደሚሆን የሚወስኑት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች በመሆናቸው ሳቢያ ሁኔታው ስላልተዋጠላቸው" አስቀድመው ከምርጫው ሂደት ራሳቸውን ማግለላቸውን ልብ ይሏል!) "ከዝንጀሮ ቆንጆ ማንን ይመርጡ" ዓይነት ቢሆንም፤ ፓርቲው ግን የተሻለውን መጥፎ በመምረጥ ከሁከት ጋር ያሰረውን የጋብቻ ቀለበት ዛሬም አለማውለቁን በይፋ ነግሮናል።

በሌላ በኩልም የአንድነት የወደፊት ትልም የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ተላላኪ ሆኖ በቀለም አብዮት ስልጣን ላይ የመውጣት ቀቢፀ-ተስፋ ያነገበ መሆኑን በገሃድ አሳይቷል–ምርጫው። ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ኢንጂነሩ በሶስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ወቅት ያሳዩት የቀለም አብዮት ተላላኪነት "ብቃት" /መቼም ተላላኪነትን 'ብቃት' እንበለው እንጂ ሌላ ምን ይባላል?!/ ለተመራጭነታቸው ሌላኛው ምክንያት ይመስለኛል። ለምን ቢባል ሰውዬው እንደ የመፅሐፍ ቅዱሱ ጴጥሮስ ኢየሱስን ሶስቴ እንደካደው ባያደርጉም፤ለአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች የቀለም አብዮት ፍላጎት ተገዝተው የገዛ ሀገራቸውን ህዝብ ዶሮ ሳይጮህ ሁለቴ ስለካዱት ነው። ምናልባትም ጊዜ ካሳየን ሶስተኛውን ክህደት በምርጫ 2007 ላይ እንመለከተው ይሆናል።…

እዚህ ላይ ግን አንድነት ፓርቲ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ የፈጠረው እንደመሆኑ መጠን፤ በፖለቲካው መስክ የመደራጀት መብት የኢትዮጵያዊን ብቻ መሆኑን አውቆ በራሱ የመተዳደሪያ ደንብ ተመርቶ ምርጫ የማካሄዱ ተገቢነት የሚያጠያይቅ አለመሆኑን ውድ አንባቢዎቼ እንደምትረዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ለምን ቢሉ በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ ተደራጅቶ የራሱን ምርጫ ማካሄድ ህገ መንግስቱ የሰጠው መብት ስለሆነ ነው። እናም ፓርቲው ባካሄደው ምርጫ አግባብነት ላይ አንዳችም ተጠየቃዊ ምልከታ የሌለኝ መሆኑ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ። ይሁንና ፖርቲው በምርጫው ሂደት ላይ እንደለመደው በውጭ ሃይሎች ሞግዚትነት የፖለቲካ ተግባሩን ለማካሄድ እያከናወነ ያለው

ድርጊት ለሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ የማይበጅ መሆኑን እንደ ዜጋ ሳልገልፅ ማለፍ አልፈልግም።

ስለ አንድነት ፓርቲ ምርጫ መሳይ ነገር በደምሳሳው ይህን ያህል ካልኩ ዘንዳ፤ አሁን ደግሞ የነገሬ ራስ ወይም ርዕስ ስላደረኩት ጉዳይ፣ ማለትም በምርጫው ላይ የአሜሪካ መንግስት ተወክሎ ስለተገኘችበት ሁኔታ ላውሳ–"የአሜሪካን መንግስት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ምን ዶለው?" የሚል ተጠየቅን በማንሳት። እርግጥ በአንድነት ምርጫው ላይ የተገኙት የአሜሪካ መንግስት ተወካይ የፓርቲው 257ኛው ስውሩ ድምፅ ሰጪ አሊያም አስመራጭ ሆነው የተሰየሙ ይሁኑ በግልፅ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፤ አንድ ዕውነታን ግን በማያሻማ ሁኔታ መግለፅ የሚቻል ይመስለኛል። ይኸውም የዋሽንግተን አስተዳደር በጋራ ተጠቃሚነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተውን እንዲሁም ከአንድ ክፍለ-ዘመን በላይ የዘለቀውን የሁለቱን ሀገራት የመንግስት-ለመንግስት ግንኙነትንና ትብብርን ወደ ጎን በማለት፤ በሀገራችን የውስጥ ፖለቲካ ሂደት በተለይም በፓርቲዎች ውስጣዊ ሁኔታ ጣልቃ የሚገባበት የትኛውም ህጋዊ አሰራር የማይፈቅድለት መሆኑን ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ግልፅ ጣልቃ ገብነት ጠንካራ ዴሞክራሲን ገንብቻለሁ ከምትለውና 'በሀገራት ህጋዊ አሰራር መሰረት የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪክ ማህበራትና ሌሎች የዴሞክራሲ ተቋማት በነፃነት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል' እያለች ከምትሰብከው አሜሪካ ፈፅሞ የሚጠበቅ አይደለም። እጅግም የሚያስገርም ነው። የግርምታውን ደርዝ ከፍ የሚያደርገው ደግሞ አሜሪካን የሚያክል ትልቅ ሀገር ከአንድ ሀገር ተራ የፖለቲካ ድርጅት ጋር /ለዚያውም ከአሮጌ አሉባልታዎች በስተቀር የጠራ የፖለቲካ መስመር ከሌለውና አመራሮቹ በየጎዳናው ላይ በአጠና ሲናረቱ ከነበሩ እንዲሁም በየሚዲያው ዱላ ቀረሽ በሆነ የስድብ ናዳ የሚዛለፉ ወገኖች/ አስመራጭ ሆና መገኘቷ ምናልባትም ከቀለም አብዮት ጋር የተሳሰረ ጉዳይ ሊኖረው ይችላል የሚል ጥርጣሬን ስለሚያጭር ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ ሃቁን ይገነዘቡ ዘንድ፤ 'ለመሆኑ የቀለም አብዮት ምንድነው?፣ ዕውን የአሜሪካ መንግስት በህዝብ ፍትሐዊ ድምፅ ተመርጠው ነገር ግን የተለየ ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ስርዓትን የመረጡ መንግስታትን በቀለም አብዮት በመገልበጥ ተግባር ውስጥ ሚና ይኖረው ይሆን? እንዲሁም ሀገሪቱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጣዊ አሰራር ውስጥ እጇን መዶሏ ዴሞክራሲን እንደግፋለን ከሚል መንግስት አኳያ

እንዴት ይታያል?' የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ምላሽ መሻት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ምክንያቱም የጥያቄዎቹ አንኳር ምላሾች የዋሽንግተን አስተዳደር ለምን በቀለም አብዮት ናፋቂው አንድነት ፓርቲ ምርጫ ላይ ፍንትው አድርገው ስለሚያሳዩን ነው።…ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው የቀለም አብዮት ማለት ከራሳቸው ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና ውጭ የሌሎችን መስማትና ማየት የማይፈልጉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች በአንድ ሀገር ውስጥ የህዝቡን ጥቅም ሳይሆን የእነርሱን ፍላጎት የሚያሳካ ተላላኪ ወይም አሻንጉሊት መንግስት ለመመስረት የሚያደርጉት ጣልቃ ገባዊ አካሄድ ነው። በዚህ ተግባር ላይ የሚሰማሩት አብዛኛዎቹ የቀለም አብዮት "ቢሊሚሎች" እንደ አሜሪካዊው ዲታ ጆርጅ ሶሮስ ዓይነት ግለሰቦች አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ ዋነኛ ግባቸውም በምዕራቡ ዓለም የሚኖረውን ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ህዝብ (99%) ሳይሆን፣ አንድ በመቶ (1%) የሚሆኑት እንደ ሚስተር ሶሮስ ዓይነቶቹን ባለረብጣዎች ተጠቃሚ የሚያደርገውን የኒዮ-ሊበራል ስርዓት ልዕልናን ማረጋገጥ ነው።

የቀለም አብዮት በባህሪው በአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎቹ የሚካሄድ ሲሆን፣ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈለገው ደግሞ ሀገር ውስጥ ባሉ እንደ አንድነት ያሉ የስልጣን ጥም ያሳበዳቸው ተቃዋሚዎች አማካኝነት ነው። በዚያች ሀገር ውስጥ የቀለም አብዮት እንዲካሄድ ምቹ መደላድል ለመፍጠርም በቅድሚያ ለምዕራባዊያን ፖሊሲዎች ገቢራዊነት የቆሙ ተላላኪ ተቃዋሚዎችን ስም ማንቆለጳጰስ ይጀምራሉ—በውጭ የሚገኙት የቀለም አብዮት አባቶች። የስልጣን እርካብ ላይ እነዚህ ፅንፈኛ ሃይሎች ሽኮኮ ብለው ተሸክመዋቸው የሚወጡ የሚመስላቸው የሀገር ውስጥ ጉምቱ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችም የገዛ ህዝባቸውን አክብረው ከመንቀሳቀስ ይልቅ፣ አቤትና ወዴት ማለትን ስራቸው ያደርጉታል። የእነርሱ ሁነኛ ታማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥም በሚያደርጓቸው ማናቸውም ተግባራት ውስጥ ምክር ይጠይቃሉ። የተሰጣቸውን "ተልዕኮ" ለመፈፀምም በእውር ድንብሩ በመንቀሳቀስ ዜጎቻቸውን እርስ በርሳቸው ከማባለት ወደ ኋላ አይሉም— ዋነኛ ዓላማቸው "የትም ፍጪው ስልጣኑን ብቻ አምጪው" የሚል ነውና።

ከዚህ ጎን ለጎንም የሊበራሊዝምን አጀንዳ የሚያቀነቅኑት ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች የቀለም አብዮት እንዲካሄድባት የምትፈለግ ሀገርን ስም ጥላሸት በመቀባት ከፍተኛ ሽፋን እንዲሰጡ ይደረጋል። እነዚህ ሚዲያዎች የቀለም አብዮቱ በህዝቡ ፍላጎት የተነሳ በማስመሰል በስፋት ይደሰኩራሉ። እናም የዚያች ሀገር ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣

የፖለቲካ ምህዳር መጥበብና መስፋት እንዲሁም ተቃዋሚዎች ያሉበት ሁኔታ ተጣምመው፣ ተንጋደውና ጎብጠው ይቀርባሉ። በምስክርነትም እነዚሁ የሀገራቸውን ክብርና የህዝባቸውን ፍላጎት አሽቀንጥረው የጣሉ ሆድ-አደር ተቃዋሚዎች የውሸት ካባቸውን ደርበው እንዲናገሩ ይደረጋል–"የዓይጥ ምስክር ድንቢጥ" እንዲሉ አበው።

እርግጥ የቀለም አብዮት በአመዛኙ የሚካሄደው በምርጫ ወቅት ነው። ምክንያቱ ደግሞ እነዚያ "ሞትኩ ለስልጣን" ባይ ተቃዋሚ ተብዬዎች በምርጫው ወቅት ልክ እንደ ኢንጂነር ግዛቸው የ97ቱ ዓይነት "የምርጫው ተጭበርብሯል" ዓይነት ድራማ እንዲከውኑ ቀጭን ትዕዛዝ ስለሚሰጣቸው ወቅቱ አመቺ ነው ተብሎ ስለሚገመት ነው። ሁከት ከተነሳም ህዝቡ እንዳስነሳው አድርጎ ለማውራት ስለሚያመች ነው። እርግጥ ለገዛ ዜጎቻቸው ኃላፊነት የማይሰማቸውና በሰዎች ደም በአቋራጭ ቤተ-መንግስት መግባት ብቻ የቀንና የሌሊት ህልማቸው የሆነው የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎች እሳቱን አቀጣጥለውት ወላፈኑን ባህር ማዶ ሆነው የሚሞቁት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ባስነሱት የቀለም አብዮት አማካኝነት የሚሞተው ሰው ምናቸውም አይደለም። እንዲያውም ከምግባራቸው ጋር የማይገናኘውን የሰብዓዊ መብትና የግጭት ፈቺዎች ነን ባይ ካባን በደረቡ ዋነኛዎቹ የቀለም አብዮት አቀጣጣይ ባልደረቦቻቸው አማካኝነት በሁኔታው እየሳቁና እየተሳለቁ በመደጋገም ይጠቀሙበታል።…

ስለ ቀለም አብዮት በግርድፉ ይህን ያህል ካልኩ ዘንዳ፤ እስቲ አሁን ደግሞ 'ዕውን የዋሽንግተን አስተዳደር በእንዲህ ዓይነቱ የመንግስት ግልበጣ ውጤት ባለው የቀለም አብዮት ተግባር ይሳተፍ ይሆን?' ወደሚለው ሌላኛው ምልከታዬ ልውሰዳችሁ።…በተለያዩ ወቅቶች የወጡ ጥናቶች እንዳረጋገጡት የቀለም አብዮት በምዕራብ ሀገራት የሚመሩ ናቸው። ስቴፈን ጎዋስ የተባሉ አጥኚ የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ "ከቀለም አብዮት መማር" በሚል ርዕስ ባቀረቡት መጣጥፋቸው ላይ በግልፅ እንዳመላከቱት፤ በሰርቢያ፣ በዩክሬንና በጆርጂያ የተካሄዱ የቀለም አብዮቶች ምዕራብ- መራሽ መንግስታትን የፈጠሩ ናቸው ይላሉ። ተጠያቂነታቸውም ለራሳቸው ህዝብ ሳይሆን ለዋሽንግተን አስተዳደርና ለምዕራቡ ዓለም የንግድ ፍላጎት እንደሆነ በማከል ጭምር። ይህ በመሆኑም የቀለም አብዮቶቹ ሁሉን አቀፍና ተቀባይነት ያላቸው እንዲሁም ተታታይና ዴክራሲያዊ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም ባይ ናቸው። ይህ እሳቤያቸውም በቀለም አብዮት እንቅስቃሴና አፈፃፀም ውስጥ የአሜሪካና ሌሎች ምዕራባዊያን ሀገሮች እጅ እንዳለበት የሚያስረዳ ነው።

እንደ ሚስተር ጎዋስ አባባል፣ ከዚህ በምዕራቡ ዓለም ውስጥ "ውግዝ ከመአርዮስ" ሆኖ በማይተገበረው የቀለም አብዮት ተጠቃሚዎች የሀገሬው ህዝብ አይደለም። ተጠቃሚዎቹ በህዝብ የተያዙ ሃብቶችን ወደ ግል ለማዞር፣ በዝቅተኛ ክፍያ የሀገሬውን ጉልበት ለመበዝበዝ፣ ለምዕራቡ ዓለም ባለሃብቶች ዝቅተኛ ታክስ የሚከፈልበት ምህዳር ለመፍጠር፣ የምዕራቡን ወጪ ንግድ ላኪዎች ለማስደሰት ሲባል ታሪፍንና መንግስታዊ ድጋፍን ለማስወገድ እንዲሁም የአሜሪካን የመከላከያ መስሪያ ቤትን (pentagon) ለማስደሰት ሲባል ከሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (NATO) ጋር ስምምነት እስከመፈራረም ድረስ እንዲደረስ የሚሰሩት የኒዮ-ሊበራል መንግስታት ናቸው። ዳሩ ግን ምዕራባውያን የፈጠሯቸው እነዚህ መንግስታት በቀለም አብዮት ከገለበጧቸው መንግስታት የተሻሉ ሳይሆኑ የባሱ ሆነው ነው የተገኙት። ለአብነት ያህል በቀለም አብዮት ስልጣን ላይ የወጡትና ዴሞክራሲያዊ ይሆናሉ ተብለው የተጠበቁት የሰርቢያ፣ የጆርጂያና የዩክሬን መንግስታት ከቀደምቶቹ የባሱ ሆነው ተገኝተዋል። በተለይም በሰርቢያና በዮክሬን ስልጣን የተቆናጠጡት መንግስታት የለየላቸው ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ልማት ሆነው በህዝባቸው ተተፍተው እንደከሰሙ የሚዘነጋ አይደለም።

ያም ሆነ ይህ አሜሪካ በቀለም አብዮት ውስጥ እጇ እንዳለበት የሚያስረዳ አንድ አስረጅ ልጥቀስ–የጆርጂያውን "የፅጌረዳ የቀለም አብዩት"። ጆርጂያ ውስጥ የቀለም አብዮት በተካሄደበት ወቅት ወደ ስልጣን እንዲመጡ የተደረጉት የጆርጅ ደብሊዮ ቡሽ አድናቂ የነበሩትና አሜሪካ ውስጥ የተማሩት ጠበቃው ሚካኢል ሳካሺቪሊ ናቸው። እኚህ ሰው እንደታሰበው አዲስና የዴሞክራሲ መንገድን ሲከተሉ አልታዩም ። ይልቁንም ሰውዬው ሀገራቸውን እጅግ በተንጠራወዘ የዴሞክራሲ ሂደት ውስጥ ከማስገባት ባለፈ፣ ለአሜሪካ ኩባንያዎችና መከላከያ ፍላጎቶች አሳልፈው በመስጠታቸው ይወቀሳሉ። ታዲያ ይህ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየን ነገር ቢኖር፣ ሰውዬው የቀለም አብዮቱን እንዲያካሂዱ በአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎችና በዋሽንግተን አስተዳደር የተመለመሉ መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ምስኪኑ የጆርጂያ ህዝብ የራሱን ጥቅም የሚያስከብርለትን እንጂ፣ አህጉር ተሻግሮ የአሜሪካን መንግስት ፍላጎት የሚያሟላ መሪ ሊመርጥ የሚችልበት ምንም ዓይነት አመክንዮ ሊኖረው ስለማይችል ነው።

እርግጥ የቀለም አብዮት አቀጣጣይ መሆናቸው በግልፅ የሚታወቁት እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ፣ ኢንተርናሽናል ሪቨርስ፣ ሲፒጄ…ወዘተ.

የመሳሰሉ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎችን ማን ወደ ሌሎች ሀገራት እንደሚልካቸው ይታወቃል። አዎ! ቀጣሪዎቻቸው ናቸው—ቢሊዮነሩ አሜሪካዊ ገንዘብ ለጋሽ ጆርጅ ሶሮስ እንዲሁም ስሙና ተግባሩ የማይተዋወቀው "የኢ-ሁከት ድርጊትና ስትራቴጂ መተግበሪያ ማዕከል" ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ቡድኖቹ የአሜሪካው "ታላቁ ነባር ፓርቲ" (GOP) /የሪፐብሊካን ፓርቲ/ ዓለም አቀፍ ክንድ መሆኑ የሚነገርለት "ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት" እንዲሁም ተቀማጭነቱ አሜሪካ የሆነውና አብዛኛውን ገቢውን ከዋሽንግተን መንግስት የሚያገኘው ብሎም ከሲ.አይ.ኤ. ጋር ቁርኝት ካለው "ፍሪደም ሐውስ"ን ከመሳሰሉት ተቋማት ገንዘብ ያገኛሉ። ታዲያ በእኔ እምነት ከእነዚህ ሃቆች በመነሳት አንድ ዕውነታን በእርግጠኝነት መናገር የሚቻል ይመስለኛል– የአሜሪካ መንግስት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በተለያዩ ሀገራት ውስጥ "በጋሻ ጃግሬዎቹ" አማካኝነት በሚከናወኑ የቀለም አብዮት ክንዋኔዎች ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንደሚሳተፍና እንደሚደግፍ።

አዎ! መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአሜሪካ መንግስት በሚደግፋቸው የቀለም አብዮቶች የሚሳተፉት ዋነኛ ተዋንያኖች፤ ሶሮስ ፋውንዴሽን፣ ዩኤስኤይድ፣ ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ፣ ዘ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት፣ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ፎር ኢንተርናሽናል አፌይርስ እና ፍሪደም ሃውስ የተሰኙት አሜሪካዊ ተቋማት ከዋሽንግተን አስተዳደር ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ የቀለም አብዮቱን በአባትነት እየመራ ያለው ማን እንደሆነ በይፋ የሚናገሩ ይመስለኛል።

እናም በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት ለበጎ አድራጎት ተግባራት የተቋቋሙትን እንደ "አልበርት አንስታይን ኢንስቲትዩት" ዓይነት ተቋማትን ሳይቀር ለቀለም አብዮት ተዋንያንን ስልጠና እንዲሰጡና የተለያዩ ጥናታዊ ፅሑፎችን በጉዳዩ ዙሪያ እንዲዘጋጁ በማድረግ ተዘዋዋሪ ድጋፍ እንዲሰጡ ያደርጋል የሚባለው የአሜሪካ መንግስት፤ በቀለም አብዮት ክንዋኔ ውስጥ አልሳተፍም የሚል አይመስለኝም። ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን ሃቆች ማንነቱን በገሃድ ይመሰክራሉና። በመሆኑም ከመሰንበቻው የዋሽንግተን አስተዳደር የቀለም አብዮት ናፍቆት ልቡ የጠፋውንና ስልጣንን ከህዝብ ድምፅ ሳይሆን በጎዳና ላይ ነውጥ ለማግኘት በሚቋምጠው አንድነት ፓርቲ ምርጫ ላይ ተገኝቶ በስውር መራጭነት ወይም አስመራጩነት መገኘቱ 'ነገሩ እንዴት ነው?' የሚያስብል ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ይህ የአሜሪካ መንግስት ተግባር ኢ-ዴሞክራሲያዊም አሳፋሪም ነው። ምክንያቱም 'በዴሞክራሲያዊ ባህል ስርፀት ውቅያኖስ ውስጥ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ ዋኝቻለሁ፣ ለሌሎችም ትምህርት እሆናለሁ' የምትለው ይህች ሀገር በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ በማን አለብኝነት ጣልቃ መግባቷ እጅግ አስደማሚ በመሆኑ ነው። ዋሽንግተን በተለያዩ ወቅቶች ዴሞክራሲን እንደምትደግፍ ስትናገር ትደመጣለች። ሁላችንም እንደምናውቀው ግን ከዴሞክራሲ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ገለልተኝነት ነው። ገለልተኝነት ደግሞ ጣልቃ ገብነትን በፅኑ ያወግዛል። ከዚህ መርህ አኳያ አሜሪካ ከጣልቃ ገብነት ባለፈ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጅ አዙር መራጭ አሊያም አስመራጭ ሆና በአንድነት ፓርቲ ምርጫ ላይ መገኘቷ ከራሷ ቀኖና ጋር እየተጋጨች መሆኑን መገንዘብ ያለባት ሆና ይመስለኛል። እዚህ ላይ አንድን ኢ-ዴሞክራሲያዊ ክስተት ሌላ ሀገር ሲከውነው "የተሳሳተ"፤ አሜሪካ ድርጊቱን እንዳሻት ስትፈፅመው ደግሞ "ትክክል" የሚሆንበት አሰራር ሊኖር እንደማይችል መረዳት ይገባል። እኔ ምንም ዓይነት ነገር ባደርግ ሁሌም ትክክል ነኝ እያሉ በዴሞክራሲ ትግበራ ላይ ለማሾፍ ካልሆነ በስተቀር። እናም ከዳበረ ዴሞክራሲ ባህሏ አኳያ ዴሞክራሲን ማስተማርና ተሞክሮዋን ለሌሎች ከተጨባጭ ሁኔታቸው አንፃር ማካፈል ያለባት ይህች ሀገር መልሳ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ ውስጥ እጇን ማስገባቷ አሳፋሪ ነው፤አሳዛኝም ጭምር።

የኢትዮጵያ መንግስት በአሜሪካዎቹ ዴሞክራትና ሪፐብሊካን ፓርቲዎች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባው ሁሉ፤ የዋሽንግተን አስተዳደርም በአንድነት፣ በመድረክም ይሁን ቅጥ አምባሩ በጠፋው ሰማያዊ ፓርቲ ውስጥ ገብቶ መፈትፈት የሚችልበት ዓለም አቀፋዊም ይሁን የሁለትዮሽ ግንኙነት ህጋዊም አሰራሮች አይፈቅዱለትም። ምንም እንኳን የአሜሪካ መንግስት ከሀገራችን ጋር በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ፣ ቀጣናዊና የሁለትዮሽ የጋራ ተጠቃሚነት ትብብር ጠንካራ ግንኙነት ያለው ቢሆንም፤ ይህ ጠንካራ መሰረት ያለው ግንኙነት እን ሁል ጊዜው ሁሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጉዳይም አንዱ ሌላውን በማክበር ላይ በተመረኮዘ ሁኔታ መከናወን መቻል አለበት። እንደሚታወቀው የኢትዮ-አሜሪካ ግንኙነት እስካሁን ድረስ በጎ ጅምሮችንም ይዞ ዛሬ ላይ የደረሰ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት በፅኑ መሰረት ላይ ተገንብቷል፡፡ ይህ ፅኑ ግንኙነትም የየሀገራቱን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ በፖሊሲና በመርህ የሚመራ እንዲሁም በመከባበርና በጋራ ጥቅም ላይ የተገነባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ

እንዳሻው እጁን የሚዶልበትን ሁኔታ አይፈቅድም፤ የጌታና ሎሌ ግንኙነትንም አያስተናግድም። እናም በእኔ እምነት ዋሽንግተን ከዚህ ወርቃማ ግንኙነት ዘልላ የውስጥ ጉዳያችንን ያልበላውን ቦታ ልታክለትና የቀለም አብዮት ሰሰኞችን ልታስመርጥበት እየተከተለችው ያለው ገሃዳዊም ይሁን ህቡዕ ጣልቃ ገባዊ አካሄድ የሁለትዮሽ መተማመንን የሚያደፈርስ ይመስለኛል።

ያም ሆነ ይህ ግን ምናልባት ዋሽንግተኖችም ይሁኑ በውጭ ሃይሎች የሚዘወር ዴሞክራሲና ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ያለ የሚመስላቸው ጥቂት የሀገራችን ተላላኪ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የቀለም አብዩት በኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰት የሚችልበት ምህዳር እንደሌለ እንደሚከተለው በማስረገጥ ፅሑፌን ልቋጭ። አዎ! የቀለም አብዮት እዚህ ሀገር ውስጥ የሚከሰትበት ቀዳዳ የለም። ምክንያቱም የስልጣን ባለቤት የሆኑት የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተቃዋሚዎችን ኢ-ህገ-መንግስታዊ ማንነት ቢያንስ ባለፉት ሁለት ተከታታይ ምርጫዎች በሚገባ ስለሚያውቅ ነው። እነዚህ ተቃዋሚዎች በምርጫ 97 ወቅት ይህን ህዝብ ከመጤፍ ባለመቁጠር የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎችን ተልዕኮ አንግበው ከህገ-መንግስቱ አግባብ ውጪ ሙከራ ማድረጋቸውን እንዲሁም በምርጫ 2002 ወቅት የቀለም አብዮት ሙከራቸው አልሳካ ሲላቸው፣ በቀጥታ ከህገ-መንግስቱ ጋር በመላተም በየኤምባሲው የማመልከቻ ዶሴ ይዘው እየዞሩ ስልጣንን ከውጭ ሃይሎች ለማግኘት ሲጧችሩ እንደነበር ከህዝቡ የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። እናም በዚህ ፍትሐዊና ሚዛናዊ ህዝብ ሁለንተናዊ ምልከታ ሳቢያ የቀለም አብዮት ምህዳር በሩ የተከረቸመ መሆኑን መረዳት ያሻል። መቼም ላይከፈት የተጠረቀመ መሆኑንም ጭምር።...

.